# ከመጋረጃው በስተጀርባ !

## ክፍል ሁለት

ከሰኢድ ማዛመድ

በክፍል አንድ በቀረበው ጽሁፍ ሂዩማን ራይትስ ዎች ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያን በሚመለከት 'ጥናት' በሚል ስያሜ ያወጣቸው የተለያዩ ዘገባዎች የመረጃ አሰባሰብና አወሳሰድ ክፍተት ያለባቸው፤ ተጨባጭ ነገርን ማሰረት ያላደረጉ፣ በፈጠራና በአሉባልታ ላይ ተመስርተው የተሳሳተ ድምዳሜ የሚሰጡ መሆናቸውን ለማየት ተሞክሯል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ መረጃን ለማሰባሰብ ተቋሙ ተጠቀምኩ የሚለው ቃለምልልስ ብቻ ሲሆን በዚሁ የተሳተፉት አካላት አመራረጥ የጥናትና የምርምርን ደንብና ስርዓት ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ ቁጥሩም ጥናቱ የሚካሄድበትን ህዝብ መወከል የማይችል መሆኑ ሪፖርቱን ያነበበ ማንኛውም ሰው የሚገነዘበው ጉዳይ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ በመረጃ ምንጭነት የተገለጹት ተዓማኒነት የጎደላቸው፤የጥቅም ተጻሮ ያላቸውና አንዳንዶቹም ማንነታቸው የማይታወቅ የምናብ ሰዎች በመሆናቸው በጥናት ስምና ፎርማት የሚወጣው የሂዩማን ራይትስ ዎች ዘገባ ጥናት ሳይሆን ተራ አሉባልታ እንደሆነ ለመቃኘት ችለናል።

ሪፖርቱ ከፍተኛ ትኩረት ከሰጣቸው ዋና ዋና ነገሮች መካከል አንዱ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እየተገነቡ ባሉ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ነው፡፡ በእነዚህ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ላይ አነጣጥሮ ካነሳቸው ነጥቦች አንዱ የኢትዮጵያ መንግስት ከነዋሪዎች ጋር ምንም ዓይነት ምክክርና ወይይት ሳያደርግ ህዝቡ ቀየውን እንዲለቅ እያስገደደ መሆኑን የሚገልጽ ይገኝበታል፡፡

በተለይ ከታችኛው ኦሞ ጋር ተያይዞ የተነሳው ደግሞ በአካባቢው በሚገነባው የስኳር ፋብሪካ ምክንያት ከአካባቢው የሚነሱ የሞርሲና የሞሬ አርብቶ አደሮች ማንነት ይቀየራል፤ ለተሟሟዪዎችና ለጎብኚዎች የነበራቸው አመች የአኗኗር ዘይቤ ይቀየራል ወይም በሌላ አነጋገር ይዘምናሉ የሚል ነው፡፡

በዚህ ሪፖርት ትኩረት የተሰጠው ሌላው ጉዳይ ከኢትዮጵያ ትላልቅ የልማት አውታሮች አንዱ የሆነው የግልገል ጊቤ ሶሰት ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተነሳው ነጥብ የጊቤ ሶስት ግድብ ሲጠናቀቅ

ወደ ቱርካና ሃይቅ የሚገባው የውሃ መጠን ስለሚቀንሰው በቱርካና አካባቢ በሚኖሩ ዜጎች ላይ ተጽእኖ ያመጣል የሚል ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ በትክክል ለመረዳት በሪፖርቱ የቀረበውና መሬት ላይ ያለው ተጨባጭ ነገር ምን ተመሳሳይና ተጻራሪ እንዳላቸው ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህንን ከማየታችን በፊት ግን በዚህ ዘርፍ እየተካሄደ ያለው ልማት ጋር ተያይዞ ያለው አጠቃላይ ሁኔታ፤ በዘርፉ የሚደረገው ልማት ለአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት የሚኖረው ፋይዳ እንዴት እንደሚገለጽ እና የሪፖርቱ መነሻ ምን እንደሆነ ማየቱ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ያግዛል፡፡
ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ጸጋ የታደለች አገር ነች፡፡ ከጸጋዎቿ አንዱ ሰፊ ለም መሬቷ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ተስማሚ የአየር ንብረት አላት፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለስኳር ልማት አመቺ እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ አገሪቱ ድህነትን ታሪክ ለማድረግና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በምታደርገው ጥረት ለልማቷ መፋጠን ወሳኝ ሚና ከሚኖራቸው የልማት ዘርፎች አንዱ የስኳር ልማት ተደርጎ የተወሰደውም ከዚህ አንጻር ነው፡፡ ለዚህ ዘርፍ እያደረገች ያለው ኢንቬስትመንት መግዘፍም ከዚህ የመነጨ ነው፡፡ ለዚህም ነው አገሪቱ በዋናነት ከያዘቻቸው የልማት ዘርፎች አንዱ የስኳር ልማት ነው የሚባለው።

የስኳር ልማት በአገራችን ከተጀመረ ከ57 ዓመታት በላይ ቢያስቆጥርም ተገቢው ትኩረት ካልተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ እንደነበርም ይታወቃል። ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅምና በተለይም እያደገ የመጣውን ፍላጎት የተገነዘበው የኢትዮጵያ መንግስት ከጥቂት ዓመታት በፊት ባለቤት እንዲኖረው በማድረግ ወደስራ ገብቷል፡፡

በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ እንደሰፈረው በዚህ ዘርፍ በአምስት ዓመት ውስጥ 10 አዳዲስ ፋብሪካዎችን ከ80 እስከ 90 ቢሊዮን ብር በማድረስ ወጪ ለመገንባት ታስቦ ባለፉት ሁለት የእቅዱ ዓመታት ወዲህ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ተጀምሯል፡፡ ፋብሪካዎች ሲጠናቀቁ 400 ሺ ለሚደርሱ ዜጎች የስራ እድል እንደሚያስገኙ ይጠበቃል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣውን የሃገር ውስጥ የስኳር ፍላጎት የሚያረካ በመሆኑ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታስገባውን ስኳር ለማስቀረት ያግዛል፡፡ ከውጭ አገር ስኳር ለማስገባት የምታወጣውን ገንዘብ ለሌላ ልማት ለማዋል እንደሚያስችል መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከ2007 ዓም ጀምሮ ለአገሪቱ ከሚያስፈልገው የስኳር መጠን በላይ የሚሆነውን ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለለማስገባት ያስችላል፡፡ ከስኳር ልማት የሚገኘው አጠቃላይ ገቢ በሌሎች ሴክተሮች ከሚገኘው ጋር በማቆራኘት

የአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት በማስረታዊነት ለማለወጥ ያስችላል፡፡ ይህ ደግሞ አገሪቱ ከድህነት ለማላቀቅ የምታደርገወን ጥረት እወን ከማድረግ አኳያ የጎላ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

በሃገሪቱ በመካሄድ ላይ ካሉ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ሂዩማን ራይትስ ዎች ያወጣው ሪፖርት ማስረተቢስ መሆኑን ሚጋገጥ ይቻላል፡፡ ሪፖርቱ ጥቂት የሰብአዊ መብትና "የአካባቢ ጥበቃ ተከራካሪዎች" ነን የሚሉ ቡድኖችን ዋቢ አድረጎ የቀረበና ያነሳቸው ነጥቦችም በአካባቢው ካለው እወነታ ጋር ፈጽሞ የሚገናኙ እንደሆነ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ኃላፊዎች የተሰጡ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች በግልጽ ያማከታሉ፡፡ መሬት ላይ ያለው እወነታም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ሃቅ ነው፡፡

ከደቡብ ኦሞ ጋር ተያይዞ የተነሳው የመሮሲና የቦዲሪ ብሄረሰቦች ከነበሩበት ተነስተው ሌላ ቦታ ሲሰፍሩ የነበራቸው የአኗኗር ዘየ ይቀየራል፣ ማንነታቸው ይጠፋል፣ ታሪካዊ ቅርሶቻቸው ይጠፋሉ የሚል ወቀሳም ተሰንዝሯል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ሁለት ብሄረሰቦች ቋሚ የሆነ መንደር አልነበራቸውም፡፡ አርብቶ አደሮች በመሆናቸው ከአንድ አካባቢ ወደሌላ አካባቢ እየተዘዋወሩ ነበር የሚኖሩት፡፡ በመሆኑም ቋሚ ቦታና ያልተረጋጋ ኑሮ የነበራቸው ብሄረሰቦችን ቋሚ ሰፈርና የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖራቸው ለማድረግ እየተሰራ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ አካባቢ የጥቅም ትስስር ያላቸው አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮችና አስጎብኚዎች የሰጡትን የሃሰት ምስክርነት እንደ ትክክለኛ መረጃ በማስመሰል በሪፖርት መልክ ማውጣት ድርጅቱ ምን ያህል ድብቅ ዓላማ እንዳለው ያሳያል።

አንድ ጥናት ሲጠና የሚጠናበት አካባቢ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ በወል መዳሰስ ይኖርበታል፡፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለው ተቋም ግን ይህንን ለማድረግና እወነታወን አወቆ ትክክለኛ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያደረገው ምንም ዓይነት ጥረት የለም፡፡ የተቋሙ ሪፖርት ተቀብለው እያራገቡ የሚገኙ አንዳንድ ሚዲያዎችም ወደ ቦታው ሄደው ያለወን ሃቅ በተጨባጭ ለማየት አልከጀሉም፤ ወይም ሆን ብለው አልፈለጉም። እያራገቡ ያሉት በስማ በለወና በሃሰት የተጠናቀረወን ሪፖርት ባለበት ደረጃ ወይም "እንደወረደ" በስፋት ማስተጋባት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሂዩማን ራይትስ ዎች ከመጋረጃው በስተጀርባ ከሚያራምዳቸው አጀንዳዎች መካከል የአንዱ ማለጫ ነው፡፡

መንግስት የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ በተረጋጋና በተሻለ ሁኔታ እንዲኖር የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ፕሮግራሞች ነድፎ ተግባራዊ በማድረጉ ተጨባጭ ለወጥ እያመጣ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከዚህም ጋር ዜጎችን ተጠቃሚ ያደረጉ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም ነው ቀደም ሲል ኢትዮጵያን አስሜልክቶ የተሳሳተ አቋም ይዘው የነበሩ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሃገራት እየሚራቸውም ቢሆን አሁን አሁን ኢትዮጵያ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት እያስማዘገበች እንደሆነ በተገኘው መድረክ ሁሉ ለመመስከር የተገደዱት፡፡

ከአርብቶ አደሩ አኗኗር መቀየር ጋር ተያይዞ እየተነሳ ያለው ወቀሳ የመነጨው በአካባቢው ለረጅም ጊዜ በህዝቡ ስም እርዳታ እያሰባሰቡ ለመኖር የሚፈልጉ አንዳንድ የእርዳታ ድርጅት ተወካዮች፡ በተንደላቀቀ ኑሮ እየኖሩ ኢትዮጵያ ወስጥ ያለው የህዝብ አኗኗር ሳይቀየር ባለበት እንዲቀጥል የሚፈሹና ከዚህም ጋር የማህበረሰብ ጥናቶችን አደረግን/እናድርግ በሚል ገንዘብ ማግኘት የሚፈልጉ አንዳንድ ቡድኖች፤ በተለያየ ጊዜያት እየማጡ በአገራችን መዝናናት የሚፈልጉ ጎብኚዎችና ከዚሁ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሆኑ አስጎብኚዎች ሰጡ የተባለውን አስተያየት በማካተት ሂዩማን ራይትስ ዎች የሰብአዊ መብት ጥሰት እንደተፈጸመ በማስመሰል በሪፖርት መልክ ማውጣቱ ማስረታዊ ስህተት ነው፡፡

ሂዩማን ራይትስ ዎች ከዚህ በተጨማሪ በአገሪቱ በተፈጠረው የህዝብ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነት ማስረት በምርጫ ተወዳድረው ወደ ሃላፊነት መምጣት ያልቻሉ የከሰሩ ፖለቲከኞችንና አንዳንድ ጽንፈኛ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች አባላት በሚፈላለግ አገሪቱን የሚወክሉ በማስመሰል አጠናቅሮ በማቅረብ የአገሪቱ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ጉዞ ላይ አሉታዊ ጫና ለማሳደር ከመጣር አልፎ ለማስናከል እየሰራ ይገኛል፡፡

እስካሁን ከቀረበው አስረጂ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር ሂዩማን ራይትስ ዎች ለኢትዮጵያውያንም ሆነ ለሌሎች ታዳጊ አገራት ህዝቦች መብት ተቆርቁሮና አስቦ የሚያደርገው ምንም ዓይነት ነገር እንደሌለ ለማገንዘብ ይቻላል፡፡

በማስረቱ ተቋሙ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብአዊ መብት ማክበር የሚያስጨንቀው ቢሆን ኖሮ የአርሶ እና አርብቶ አደሩን ህይወት ለማሻሻል የሚያስችሉ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ጣቱን ባልቀሰረ ነበር፡፡ እነዚህን የልማት ተቋማት የህዝቡን ሰብአዊ መብት ለማጠበቅ የሚያስችሉ በመሆናቸውም በደገፋቸው ነበር፡፡ ህዝቡ በአንድነት ለልማት በሚነሳበት ወቅት የተለያየ የህዝቡን ስሜት ይጎዳል ያለውን ነገር ሁሉ እየሰበሰበ ሜራገቡንም ባልቀጠለበት ነበር፡፡

ከ85 በመቶ በላይ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚኖረው በገጠር ሲሆን የሚተዳደረውም በእርሻ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ህዝብን ኑሮ ለማሻሻል አርሶና አርብቶ አደሩ ላይ ሰፊ ስራ ማሰራት የግድ ይላል፡፡ አርብቶ አደሩ አንድ ቋሚ መኖሪያ ሰፈር የለውም፡ ውሃና ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ነበር ነው የሚኖረው፡፡ ይህ አይነቱን አኗኗር ለትምህርትና ጤና አገልግሎት ተደራሽነት አመች ባለመሆኑና አርብቶ አደሩም የተረጋጋ ህይወት እንዲኖረው ስለሚያደርግ ይህንን ለመቀየር መንግስት ሁለት መንገዶችን ተከትሎ እየሰራ ይገኛል፡፡ አንደኛው ተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶችንና የጤና ተቋማትን ማቋቋም ሲሆን ሌላው ደግሞ አርብቶ አደሩን በመንደር ማሰባሰብ ነው፡፡

አርብቶ አደሩ በመንደር በማሰባሰብ ማንኛውንም አገልግሎት በቀላሉ እንዲያገኝ ከማስቻሉም ባሻገር የተረጋጋ ህይወት ለመምራት እንዲችል ለማገዝ በተለይም በአራት ክልሎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት ነው፡፡

ሂዩማን ራይትስ ዎች ግን ለዚህም ሌላ አቃቂር አወጥቶለታል፡፡ መንግስት አርብቶ አደሩን ወደ ዘመናዊ ህይወት ለመቀየር እየሰራ በመሆኑ የአርብቶ አደሩን የአኗኗር ዘየ እየቀየረው ነው፡ ማንነቱን እያጠፉ ነው በሚል፡፡ ለምን በመንደር ይሰባሰባሉ? ይህ ሰብአዊ መብታቸውን መተላለፍ ነው ሲልም አስቂኝ ወቀሳውን ቀጠለ፡፡ እንደለመደውም የኢትዮጵያ መንግስት ህዝቡን በማስገደድና ሰብአዊ መብቱን በመተላለፍ የሰፈራ ፕሮግራም እያካሄደ በመሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማንኛውም እርዳታ እንዳያደርጉለት ሲል ተማጠነ፡፡

እንግዲህ ይህ ድርጅት የሰብአዊ መብት ተሟጋች ከሆነ እነዚህ ሰዎች የትምህርት እድል ማግኘት አለባቸው፤ የጤና አገልግሎት ሊስፋፋላቸው ይገባል፡ ከአገሪቱ የልማት ለውጥ እነሱም ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፤ ከኋላ ቀር ኑሮ መላቀቅ አለባቸው ማለት በተገባው ነበር፡፡ እየሰማን ያለው ግን ለምን ከኋላቀርነት ይላቀቃሉ የሚል ነው፡፡ የነበራቸውን የአኗኗር ዘይቤ ለማህበረሰብ ምርምርና ለጉብኝት ጠቃሚ ስለሆነ በድህነት እየማቀቁ መቀጠል አለባቸው፡፡ የልጅ ልጆቻቸውም ዓለም በሰለጠነበት በአሁኑ ወቅት የቅድመ አያቶቹን የአኗኗር ዘይቤ ይዞ መቀጠል አለበት የሚል ነው፤ የሂዩማን ራይትስ ዎች አቋም፡፡

ልብ በሉ! ይህ ሃሳብ የማንን ፍላጎት የሚያሟላ ነው? የጎብኚዎችንና የተመራማሪዎችን ወይንስ የአርብቶ አደሩን? የኢትዮጵያ ህዝብ ከድህነት እንዳይላቀቅ፤ በኋላቀርነትና በድህነት አዘቅት ውስጥ ተዘፍቆ እንዲኖር ለማድረግ በተለያየ ሚልክ ማታገል የሂዩማን ራይትስ ዎች ህቡእ አጀንዳ ነው፡፡

አዳዲስ በማነቡትና ማከፋፈያ በሚደረግበቸው የስኳር ፋብሪካዎች ጋር ተያይዞ በሪፖርቱ የቀረበው ወንጀላ በዋቢነት የጠቀሳቸው 35 ነዋሪዎች፣ 10 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮችና ሌሎች ማንነታቸው ያልተገለጡ 30 ግለሰቦች ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ በአካባቢው በሚኖሩ አርሶ አደሮች ላይ የህብረተሰብ ጥናቶችን በሚደረግ፡ ኀብኚዎችን በማስተናገድ እና አርሶ አደሩን እንረዳለን በሚል ሽፋን ገቢ የሚሰበስቡ ድርጅቶች ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች ካላቸው ጥቅም አንጻር የአርብቶ አደሩን ማወጥ ስለሚፈልጉ ከራሳቸው የግል ጥቅም አንጻር ብቻ በማሳት ለሂዩማን ራይትስ ዎች የሃሰት ወሬ እየለቃቀሙ የሚቀርቡ ወኪሎች ናቸው፡፡

ይህ ተቋም በእነዚህ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ባሉባቸው ስፍራዎች የሄደበት ወቅት የለም፡፡ እዚያ አካባቢ ያለው ህዝብም ምን እንደሚመስልና አኗኗሩ ምን እንደሆነ ለማወቅ አልሞከረም። መንግስት ከነዋሪዎቹ ጋር ወይይት ሚድረግ አለሚድረጉን፤ ህብረተሰቡን፤የሚመለከታቸውን የአካባቢውንና የፌደራል መንግሥት የአስተዳደር አካላትንና ኃላፊዎችን እንዲሁም ባለሞያዎችን አነጋግረው ያወቁት ነገር የለም፡፡ ከምንም ተነስቶ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ መድረስና ሌሎችም ይህንን የተሳሳተ ድምዳሜ እንዲያራግቡ ሚድረግ ለአካባቢው ህዝብ መብት ማሰብ ሳይሆን የመቀየርና ከደህነት የማላቀቅ ማስረታዊ መብቱን መቃወም ነው፡፡

በስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ ምክንያት ምን ሊከሰት ይችላል የሚለው ከግንባታዎቹ መጀመር በፊት ጥናት ተካሂዶ በጥናቱ ማስረት ደግሞ ዝግጅት የተደረገ በመሆኑ ህዝቡ ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደሌለ በመንግስት በኩል ግልጽ ምላሽ በተደጋገሚ ተሰጥቶበታል፡፡ ከዋልድባ ገዳም ጋር ተያይዞ የተነሳው ነጥብ የተሳሳተ መሆኑንና የስኳር ልማቱ የገዳሙን ይዞታ የሚነካ እንደሆነም ከመንግሥት አካላት ከቤተክህነትና ከህብረተሰቡ የተወጣጣ ቡድን አረጋግጦና ህብረተሰቡም ይህንኑ በማነባ ተረድቶና አምኖበት መግባባት የተደረሰበት እንደሆነ ከእኛ ከባለቤቶቹ የበለጠ ማንም ማስከርነት ሊሰጥ የሚችል ወገን አይኖርም፡፡

ይህ ሃሰተኛ ክስ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን ገንብታ ራሷን የቻለች አገር እንድትሆን የተያዘውንና በእስካሁኑ እንቅስቃሴም ተጨባጭ ለውጥ እያሳየ የመጣውን ሃገራዊ ዕራእይ ለማክካት እየተከናወነ ያለውን ጥረት ለማፍናቅ ያለመ ነው፡፡ ይህም በሌላ ጎኑ በአንዳንድ ሃይሎች እየተሰነዘረ ያለው የጥላቻ ፖለቲካ አንዱ ክፍል ነው።

የሂዩማን ራይትስ ዎች የፈጠራ ክስና ወንጀላ በስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ዙሪያ ብቻ የተከለለ አይደለም፡፡ ሌሎች ማስረታዊ ተጻሮዎችንም ለማንሳት ሞክሯል፡፡ ከእነዚህ አንዱ የጊቤ ሶስት

የኤሌክትሪክ ሃይል ማምንጫ ግንባታን የሚሟከት ነው፡ ፡ ይህንን ደግሞ በቀጣይ ክፍል እንማከታለን።